# መ ቅ ድ ም

የሰው ልጅ ብቻውን የማይኖርና ግለኝነትም የማይገባው ፍጥረት ነው ፤ ሥነ ፍጥረትንም ስንመለከት ሰው ብቻውን ሊኖር እንደማይገባው አንዱ አንዱን ረድቶ ማኅበራዊን ኑሮ አጽንቶ መኖር እንዳለበት የሚያስረዳን ነው ፤ ይኸንም የሚያስረዳ ለጊዜው በሚስትነት ደረጃ የምትረዳው ወይም በባልነት ደረጃ የሚረዳት እንፍጠርለት ሲሉ ሥላሴ ለአዳም ወዲያው ሔዋንን ከጐኑ እንደፈጠሩለት እንረዳለን (ዘፍጥ ፪ ፲፰-፳፭) ። ፍጻሜውን ስንመለከት ግን ሰው ያለ ሰው ሊኖር የማይችል ወይም የማይገባው መሆኑን የሚያስረዳ ሁኖ እናገኘዋለን ።

ከዚህም ጋር ማኅበራዊ ኑሮ ከቤተ ሰብ እንደሚጀመር የሚያስረዳ ሁኖ እናገኘዋለን ። ይኸም በትክክል የሚያመለክተን የሰው ልጅ ሁሉ በማኅበራዊ ኑሮ እንዲጠቀም ወይም እንዲጠቅም ግለኝነትን ወይም ብቸኝነትን አጥፍቶ ከሁሉ ጋር ያለውን ዝምድናውን ግንኙነቱን አብዝቶ እንዲኖር የተደረገ ቅዱስ ዓላማ መሆኑን ነው ። የሰው ልጅ ሁሉ ግንዱ አንድ የሆነ ልዩ ልዩ ቅርንጫፍ ነው ፤ ወይም ቁጥሩ የበዛ የአንድ ዛፍ ፍሬ ነው ፤ እንዲህም ከሆነ ያላንዱ አንዱ አይደምቅም ፤ ያላንዱ አንዱ አያምርም ። ያላንዱ ርዳታ ፩ኛው ሊድን ከቶ አይችልም ፤ ግዳጁም አይፈጸምም ፤ ስለዚህም ያንዱ ፍላጎት ከአንዱ ጋር እንዲገናኝ ወይም እንዲተባበር ያደርገዋል ። በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ ጥቅሙን አውቆ ለማኅበራዊ ኑሮ ሕይወት ሰጥቶ መልክ ቀርጾ ሲሠራው ይገኛል ። የሰውም ልጅ በማኅበራዊ ኑሮ ሲተባበር ያሠለጠነ የተማረ ያሰኘዋል በእርግጥም የዚህንም ጥቅም አውቀው እንደ ዓላማው የሚፈጽሙት የሠለጠኑ ሕዝቦች የሚባሉት ሁነው ተገኝተዋል ። ስለዚህ የተፈጥሮ ውን ዓላማ የሚያውቅ በማኅበራዊ ኑሮ የሚጠቀም እውነተኛ ሰው ይባላል የሠለጠነው ሕዝብ የሚያሰኘውም ቅሉ ይኸን ተግባር በሚገባ ፈጽሞ ሲገኝ እንደሆነ ማንም ሊረዳው ይችላል ። በብቸኝነትና በዘላንነት የሚኖረው ደግሞ ያልሠለጠነ የኑሮ

ጣዕምን ያላወቀ ሕይወቱን ያልጠበቀ እየተባለ ይነቀፋል ሊባልም
ይገባዋል፤ምክንያቱም ፤ ገና ዓላማውን ያላወቀ በድንቁርና የጠለቀ እንደ
ሆነ ያለፈውን ታሪክ የጊዜውን ደግሞ የዕለት ሁናቴው ያስረዳናልና።
ጠቅላላው የሰው ኑሮ በማኅበር በመረዳዳት ሲሆን ይገባል « ጥርስና
ከንፈር ሲደጋገፍ ያምር» እንደተባለው ሰው በሰው ሲደገፍ
ሰውን ሰው ሲደግፈው በጣም ደስ ያሰኛል ። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ
እንደ ኢትዮጵያነቷ ከታወቀችበት ጊዜ ጀምሮ በማኅበራዊ ኑሮ የታወ
ቀች ሌላው ዓለም የማይጠቀምበትን ልዩ ልዩ ዘዴ ሁሉ ይዛ ስታስ
ተምር እንዲሁም አንዱ ከአንዱ የሚገናኝበትን የሚዛመድበትን ስት
ሠራ ኑራለች አሁንም ትገኛለች ፤ በዚህም ምክንያት ሰፊው ግዛት
ብዙውም ሕዝብ ሳይለያይ ኅብረቱን አጽንቶ በማኅበር ሠርቶ ይገኛል።

ጥንታውያን አባቶቻችን የሠለጠኑ እንደሆኑ ለማቅ ስንፈልግ ሕይ
ወታቸውን ለማኅበራዊ ኑሮ ሰጥተው ሲሠሩ ሲጠቀሙበት እንደኖሩ የሚ
ያመለክተውን ታሪካቸውን ማጥናት በጥብቅ ያሻል ። ከማኅበራዊ ኑሮ
አቸው ውስጥ ደግሞ ከፍ ያለውን ምዕራፍ በመያዝ የታወቀው ፤ በዝ
ክር በማኅበር መልክ እየተሰበሰቡ እየበሉና እየጠጡ እርስ በርሳቸው
እየተዋወቁ የሚፈጽሙት የነበረው ፤ በዚህም አማካይነት ድሆችን በሽተ
ኞችን ለመርዳት የሚያደርጉት መተባበርና የሚያወጣጡት አስተዋጽኦ
ብዙ ችግርን አስወግዶ ፤ ሰዎችን ረድቶ ይገኝ ነበር ። ይኸም ተግባር
ከክርስትና ሃይማኖት የተገኘ ጠቃሚነቱ ከፍ ያለ ሲሆን አንዳንዱ
ደግሞ ከጥንት ዘመን የመጣ ከኢትዮጵያውያን ደም ጋር የሠረጸ እንደ
እንግዳ መቀበል እንደ ማስተናገድ ዘመድ ዘመድ እንደማለት ያለው
ሰብአዊ ርኅራኄ ነው ። ይኸንም ጥንታውያን የሆኑ ጽርዓውያን «የኢት
ዮጵያውያን ርኅራኄያቸው እንደፈጣሪያቸው» ሲሉ አመስግነው ጽፈ
ዋል ። የዛሬው ጊዜ ሥራችን ከማኅበራዊ ኑራችን ጋር ሲመዛዘን ጥን
ታውያን አባቶቻችን በሥልጣኔው ከፍ ያሉ እንደነበሩ ማኅበራዊ
ሥራቸው ግልጥ ሆኖ ያስረዳል ወገንንም ያኮራል ።

ዛሬ እንኳን ሊሠራ የማይቻለው ተግባር በዚያን ጊዜ ቀላል ሁኖ
የእርስ በርስ መረዳዳት የእርስ በርስ መተዋወቅ ከፍ ያለውን ደረጃ
ይዞ ሲገኝ የሕዝቡ ታላቅነት የሥልጣኔው ጥንታዊነት ምን ያህል
እንደነበር ያመለክታል ። ማኅበራዊ ሥራን በዚህ መልክ አዘውትረው



ይሠሩት ስለነበር ችግርን ከሰው ልጅ አስወግደው ራሳቸውም ተደስ
ተው ይኖሩ ነበር ፤ ስለዚህም ምሳሌ ሲመስሉ «ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም
አይጎዳ » ይሉ ነበር ፤ ያለ ችግርም ይኖሩ ነበር ለማለት ይቻላል ።
ይኸንም እየተመለከትን የነዚህ ሰዎች ልጆች መሆናችንን ስናስብ
በአንድ በኩል ልንኮራ ይገባናል ፤ ምክንያቱም ጥንታውያን ሕዝቦች
እንደሆን ሥርዓትም የነበረን መሆናችንን ስንመለከት ነው ፤ በሌላ በኩል
ደግሞ አባቶቻችን ለማኅበራዊ ኑሮ ከፍ ያለ ትርጉም ሰጥተውት እንደ ከፍ
ተኛ ግዴታ ቆጥረው ሲሠሩት በማኅበራዊ ኑሮ አምነው ግዳጃቸውን
ሁሉ ሲፈጽሙ እኛ ከዚህ ርቀን አንዱ አንዱን ሳያውቀው አንዱ
አንዱን ሳይረዳው ፤ ስንገኝ በጣም ያሳዝናል ፣ ማለት ከሥልጣኔ ወደ
ኋላ የሔድን መስሎ ታይቷልና ። ሆኖም አሁን በበለጠ ለመሥራት
እንችል ዘንድ ጥንታውያን አባቶች አንዱ ከአንዱ ጋር እንዴት ይተዋ
ወቅ እንደነበር አንዱ ደግሞ ከአንዱ ጋር እንዴት ይዛመድ እንደ
ነበር አንዱ ደግሞ አንዱን እንዴት ይረዳ እንደነበርና በጠቅላላም
ማኅበራዊ ኑሮ ለኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ግምት ይሰጠው እንደነበር
የአሠራሩም ዘዴ እንዴት እንደነበር ማወቅ አስፈላጊና ጠቃሚ ስለ
ሆነ ማጥናት ይኖርብናል ፤ ከአጠናነውም ዘንድ መሥራት ግድ ስለ
ሚሆንብን አጥንተን ለሥራ እንዘጋጅ ዘንድ በመጠኑ ከዚህ እንደሚ
ከተለው ጥንታዊ ማኅበራዊ ሥራትንና ኑሮአችንን እገልጣለሁ ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

ምዕራፍ ፩ ፤

# የክርስትና ትምህርትና ማኅበራዊ ኑሮ

## ፩ ብሂል ፤

ማኅበር ማለት ኅብረ አንድ ሆነ ተባበረ ማለት ነው ፤ ይኸም ማለት የሰው ልጅ ሁሉ በኑሮው በሥራው እንዲሁም በስምና በአካል የተለያየ ሲሆን በአሳብ አንድ ሆነ ተባበረ ማለት ነው ይኸም ሁናቴ የሰውን ልጅ ጥበብ ወይም መሻሻል የሚያመለክት ነው ፤ ማለት የሰው ልጅ ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ እየዋለ እያደረ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸጋገረ ችግሩ እየገባው የአንድነትን ጥቅም ለይቶ እያወቀ ከመለያየት ይልቅ ተባብሮ መኖርና መሥራት ጠቃሚ መሆኑን እየተረዳ በኑሮ ዘላንነትን አጥፍቶ በአንድ ላይ መኖርን ጀመረ ። አብሮ ከኖረም ዘንድ ታላላቅ ታምራትን አደረገ ማለት ታላላቅ ከተማዎችን ለመሥራት የመገናኛ መሥመሮችን ለመዘርጋት የጋራ ችግርንም ለማስወገድ ቻለ ይኸም የአንድነት ኃይል የአንድነትም ትርጉም ነው ። አንድነት ኃይል ነው እንደተባለው ሁሉ የሰው ልጅ ይኸን ታላላቅ ከተማ ሁሉ ለመሥራት የሚያስችለው ኅብረትን አንድነትን ገንዘብ ስለአደረገ ነውና ። የሠለጠኑት ሕዝቦች ከብቸኝነት ወይም ከገለልተኝነት ወጥተው በመራቀቃቸው መገባባትን አብሮ መሥራትን የንግድ መለዋወጥን ገንዘብ ስላደረጉ በሀብት ከፍ ብለው የኑሮ ደረጃቸውን አሻሽለው ይደገኛሉ ። የሆነ ሆኖ ማኅበራዊ ኑሮ ሲባል አፍአዊ አብሮ የመኖርን ትርጉም ብቻ ሳይዝ በመንፈስም አንድነት ያለው ሆኖ ሁሉን የሚያገናኝ የሚያስማማ ሕግ አውጥቶ በስምምነት የሚሠሩት ሥራን የሚኖሩትንም ኑሮ የሚያመለክት ነው ።

ራሳቸውን ለመርዳት አውጥተው አውርደው የሚያደርጉት ስምምነት የሚያደርጉትም ኅብረት ማኅበራዊ ኑሮ ይባላል ። እንዲሁም የሰው ልጆች በመተባበር የሚሠሩት ለምሳሌ ድሆችን ለመርዳት በሽተኞችን ለማ

ጥተው ልዩ ክብር ባለው ልብስ አጌጡ ተሸለሙ ተጋረዱ ለማለት ተክሊል ይሉታል ፤ ጠቅላላ አገላለጡ ግን ሠርግ ካለው ቃል ጋር ይገናኛል ።

**፪/ ማጨት ፤**

ከሠርጉ በፊት የሚሆን የጋብቻ ዋዜማ የሚመስል በድግሽም ሆነ ሕዝብ በመገናኘት በጸሎቱ በጠቅላላም በሥነ ሥርዓቱ ሁሉ ሠርጉን የሚመስል ነገር አለ ፤ ይኸውም ፤

ሀ) ማጨት ነው ፤ ይኸም ማለት ሊይዘው ወይም ሊያድርበት ፈለገ ማለት ነው ፤ በዚህ መልክ እገሌ እገሊትን ሊያገባ ያጫል ይባ ላል ፤ ማለት ይፈልጋል ይመኛል ማለት ነው ፤ ሊይዛት ሊያገባት ይች ላል ሊተዋትም ይችላል ገና ልቡ አላረፈም ፤ አልቆረጠም የርሷም ቢሆን እንዲሁ ነው ።

ለ) አረቦን ፤ የሚሉት ቃል ነው ፤ ይኸም ማለት ምልክት ማለት ሲሆን ልክ ጋብቻውን የመሰለ ወይም የጋብውም መጀመሪያ ደረጃ ስለሆነ ከፍጹም ክብር በፊት ሌላ ክብር ተሰጠው ፤ ወይም ከጋብቻው በፊት ያለውን ሥነ ሥርዓት ፈጸመ የስምምነት ውልን የቃል ኪዳንን ምልክት አደረገ በማለት አረቦን ይሉታል

ሐ) የቀለበት ቀን ወይም ቀለበት ማሠር ይባላል ፤ ይኸም ሲያጩ ከኖሩ በኋላ እጮኛይቱ ይሆነኛል ወይም እርሱ ትሆነኛለች በማለት ከወሰኑ በኋላ ፤ ወይም ወላጆችና አሳዳጊዎች እገሊት ለእገሌ ትሆንለ ቃለች ለእገሊትም እገሌ ይሆናታል ብለው ከወሰኑ በኋላ የሚያደርጉት ስምምነት የሚሰጡት ቃል የሚፈጽሙት ሥነ ሥርዓት የቀለበት ቀን ወይም የቀለበት ማሠር ይባላል ።

ይኸም የአንድ ስምምነት ምልክት ነው ፤ ማለት ቀለበት አንድ የማሠሪያ የመወሰኛ ምልክት ነው እርስዋ ለርሱ እርሱም ለርስዋ ሊሆኑ በፈቃዳቸው የተሳሰሩ ቃልም የገቡ ከዚያ በኋምላ ሊያፈርሱ አይ ችሉም በማለት ቀለበት ያስሩላቸዋልና ። ይኸንም በማለት ብዙ ሽማ ግሌ ይዘው ብዙ እማኝ ባለበት ይኸንኑ ቃል ኪዳን ይፈጽማሉ ። ቀለ በትም የማስገንዘቢያ ምልክት ነው ፤ ለምሳሌ በጥንት ዘመን አንድ ሰው ወደ አንድ አገር ሲሄድ ወይም ወደ ገበያ ሲወጣ ባልንጀራው



አንድ እቃ ገዝተህልኝ ና ይለዋል ፤ እንዳይረሳም ከጣቱ የሺቦም የሳ ርም ቀለበት ያስርለታል እርሱም ያን በተመለከተ ጊዜ አንድ ቀል እኮ ወይም አደራ እንዳለበት ያምናል በየጊዜውም ይገነዘባል በዚ ህም መሠረት የታዘዘውን ይፈጽማል ። ወይም ቀለበቱ የነገሩን ብር ታት ቁም ነገረኝነቱን ያመለክታል ለምሳሌ በቀድሞ ጊዜ አንድ ሰው በተከሰሰ ጊዜ ቀርቦ ነገሩ አንድ ውሳኔ እስኪያገኝ ባለእዳ ለመሆኑ ቁራኛ ተብሎ ልብሱ ተ ቋጥሮ ምልክት ተደርጎበት ይሄድ ነበር ወይም ከሰው ጋር ተቆራኝቶ ይሄድ ነበር እርሱም እንኳን በመን ገድ ሳለ ከቤቱ ውስጥም ቢሆን ብቻውንም ቢሆን ወይም ከሰው ጋር ቢቆራኝ የሚያየኝ የለም ብሎ ዳኛው የቋጠረውን አይፈታም እንዲያ ውም በየጊዜው በአየው ልክ እዳ እንዳለበት እያሰበ ለዚያ መውጫ መንገድ ሲፈልግ ይገኛል ። የቀለበትም ማሰር ትርጉም ያን ቀለበት ከእሠሩበት ጊዜ ጀምሮ እጮኛዎቹ ቀለበታቸውን እያዩ እርሱ ለርስዋ ርእሷም ለርሱ የተሰጣጡ የተዳረጉ የተቆራኙ እንጂ አንደኛው በርሱ ፈቃድ ብቻ የሚያደርግ አለመሆኑን ያመለክታል ። ይኸንም ጽኑዕ ቃል ኪዳን መግባታቸውን በሰው ፈቃድ መጽናታቸውን እንዲ ገነዘቡ ቀለበት ያሥሩላቸዋል ፤ የቀለበት ማሰር ዕለት ይሉታል ። በአንድ በኩል ራሱ ቀለበቱ ከቀለበቱም ጋር የሚሰጠው ስጦታ እጅ መንሻ ማግባቢያ ሊሆን ይችላል ፤ ይኸም ዓይነት ስጦታ ከጥንት የቆየ በማንኛውም አገር ያለ ነው ፤ ነገር ግን በአንዳንድ አገር ገንዘ ብም ሆነ ልዩ ልዩ ሽልማት የሚሰጠው ለወንድ ነው ፤ በአንዳንዱ ደግሞ ወንዱ ለሴት ይሰጣል ፤ በኛ አገር ግን በልዩ ልዩ ጠ/ግዛቶች እንዲሁ የተለያየ ሁኖ ይገኛል ፤ ማለት በአንድ ጠ/ግዛት የሴት ወገን ለወንዱ ሙሽራ በዛ ያለ ሀብት የልብስ ሽልማት ሰጥተው ይድሩ ታል ፤ በአንዳንድ አገር ደግሞ ወንድ ሙሽራ ይኸን ሁሉ ለሴቷ ሰጥቶ ያገባል ።

መ) ፍጥምጥም ፤ ይኸም ቃል የዚህን ተግባር የሚገልጥ ሲሆን የቃሉ ፍች ደግሞ ተፈጸመ ተጨረሰ ካለው የወጣ ነው ፤ ፍጥምጥም ማለትም መጨራረስ ነገሩን መወሰን ማለት ይሆናል እንደዛሬው የሥነ ጽሑፍ ስልት ለሁሉ ስላልተሰጠ የመጻፍ ችሎታም ስላልነበር የነገሩ ፍጻሜ የመሪውን ስም በመጥራት እገሌ ይሙት በማለት ይጨ

